# 25ኛው የኦህዴድ የምስረታ በዓል በጀርመን ፍራንክፈርት ከተማ በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል!

ኦህዴድ/ኢህአዴግ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ለዘመናት የዘለቀውን የጭቆና ቀንበር በመስበር የኦሮሚያ ክልል ህዝብ መብትና ተጠቃሚነት ለማረጋግጥ መቻሉን በጀርመን አገር  የሚኖሩ አንዳንድ የኦሮሚያ ክልል ተወላጆች እና ወዳጆች ገለጹ።



በበዓሉ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የቀኑ የክብር እንግዳ በፍራንክፈርት የኢፌዲሪ ቆንስል ጄኔራል አቶ ምህረታአብ ሙሉጌታ ለኦ.ህ.ዴ.ድ. አባላትና ደጋፊዎች ለ25ኛው የድርጅቱ የልደት በዓል እንኳን አደረሳችሁ ካሉ በኋላ የክልሉ ህዝብ ለዘመናት ተነፍጎ የቆየውን በቋንቋው የመናገር፣ ባህሉን የማሳደግና የፈለገውን ሃይማኖት የማምለክ መብቱ በኦህዴድ/ኢህአዴግ መሪነት ባደረገው ትግል ማረጋገጡን ገልፀዋል።




በዕለቱ ኦህዴድን ወክለው ድርጅትዊ መግለጫ የሰጡ አቶ ግርማ ደምሴ  ከ25 ዓመት በፊት መጋቢት 17 ቀን 1982 ኦህዴድን በመመስረት የተሰራው ታላቅ ክንውን በኦሮሞ ህዝብ የትግል እንቅስቃሴ ወስጥ የጠራ መስመር ያለው አቤታዊ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅት እውን የሆነበት እና በህዝብ የዘበናት ትግል ውስጥ ተከስቶ የነበረው የሀንቀኛ መሪ ድርጅት እጦት ችግር የተወገደበት በመሆኑ ኦህዴድ የተመሰረተበት እለት በኦሮሞ ህዝብ ታሪክ ውስጥ ልዩ ስፍራ ያለው በዓል መሆኑን ገልፀዋል።



የበዓሉ ተሳታፊዎች እንደገለጹት በኦ.ህ.ዴ.ድ./ ኢ.ህ.ዴ.ግ. መሪነት ለድል የበቃው የህዝብ ትግል "ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ቤት መሆኗን እና የሁሉም የአገራችን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት በተግባር ያረጋገጠ ነው።"



በርካታ የበዓሉ ተሳታፊዎች በተጨማሪ ድርጅቱ ክልሉን የልማትና የዴሞክራሲ ስኬቶች ተጠቃሚ በማድረግ የማህበረሰቡን ኑሮ በማሻሻል በህዳሴ መስመር እንዲራመድ አስችሏል ነው ያሉት።